ጤና ሚኒስቴር-ኢትዮጵያ
የዜጐች ጤና ለሀገር ብልፅግና!

Ministry of Health - Ethiopia
Healthier Citizens for Prosperous Nation!

ቀን Date 26/09/2014
ቁጥር Ref. No. መጠ1/49/39/1047

ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
ደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
ሶማሌ ብ/ ክ/መ/ የምግብ፣መድሃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን
ቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
ጋምቤላ ክ/መ/ ጤናና ጤና ነክ ግብአቶች እና አገልግሎቶች ጥራት ቁጥጥር ኤጀንሲ
ሀረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስ/ የምግብ፣ መድሃኒት እና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን
ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ
ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ
ባሉበት

ጉዳዩ:- በመመሪያ 770/2013 ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በተመለከተ

እንደሚታወቀው የጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ስራ ፍቃድ አሰጣጥ መመሪያ 770/2013 ተዘጋጅቶና ፀድቆ ስራ ላይ እንዲውል በቁጥር መጠ1/49/39/607 በቀን 7/8/2013 በተፃፈ ደብዳቤ በተጠየቀው መሰረት በሀገር አቀፍ ደረጃ ስራ ላይ መዋሉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በሂደት በመመሪያው ያልተመለሱ/ያልተዳሰሱ ጉዳዮች በመኖራቸውና እነዚህም ጉዳዮች ከሁሉም ክልሎች ተሰብስበው የተለያዩ የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀትና የሚመለከታቸውን አካላት በማሣተፍ ከተወያየንባቸውና የተለያዩ የሙያ ማህበራትና ባለድርሻ አካላት ሀሳብ እንዲሰጡበት ከተደረገ በኋላ የመፍትሄ ሀሳብ ተቀምጦላቸዋል፡፡ በመሆኑም የተለዩትን ጉዳዮችና የተሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦች በ 6 ገፅ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እየገለፅን ከሰኔ 01/2014 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ዶ/ር አየለ ተሾመ ጎንቼ
ሚኒስቴር ዴኤታ

ግልባጭ

- ለክብርት ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሚኒስትር ዴኤታ(የስርዓት አቅም ግንባታ ዘርፍ)
- ለጤና ባለሙያዎች ብቃት ምዘናና ፍቃድ ዳይሬክቶሬት
  ጤና ሚኒስቴር

+251-115-517011
+251-115-518031
+251-115-159657
+251-115-524549
+251-115-516378
+251-115-513301
Fax +251-115-519366
1234
Addis Ababa, Ethiopia
E-mail: moh@moh.gov.et
Website: www.moh.gov.et
Ministry of Health, Ethiopia
@FMoHealth

**በጤና ባለሙያዎች ምዝገባና የሙያ ስራ ፈቃድ አሰጣጥ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 770/2013 ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን በተመለከተ የቀረቡ ሃሳቦች፡**

1. **በሁለት ሙያዎች የሙያ ስራ ፈቃድ መስጠትን እና የስራ ልምድ አያያዝን በተመለከተ፡-**

**የመፍትሄ ሀሳብ፡**

- ✓ በክሊኒካል ሙያው እየሰራ ያለ ባለሙያ MPH ተምሮ ቢመጣ፣ በሁለቱም ሙያዎች የሙያ ስራ ፍቃድ ማግኘት ይችላል።
- ✓ GP የነበረ MPH ተምሮ ቢመጣና በሁለቱም የሙያ ፈቃድ ቢጠይቅ "ፐብሊክ ሄልዝ ስፔሻሊስት" የሚለውን ጨምሮ በሁለቱም ሙያዎች የሙያ ስራ ፍቃድ ማግኘት ይችላል።
- ✓ ዲፕሎማ ነርስ የነበረ ባለሙያ ጤና መኮንን ዲግሪ ተምሮ የብቃት ምዘና ፈተና አልፎ ቢመጣ፤ በመረጠው በአንዱ ብቻ የሙያ ስራ ፍቃድ ይሰጠዋል። በዲፕሎማው መውሰድ ቢፈልግ ጤና መኮንን ትምህርት ላይ ነበርክ ተብሎ ለተግባር ልምምድ ሊመደብ አይገባውም (በትምህርት ላይ የነበረበት ጊዜ እንደ ስራ ልምድ ይቆጠርለታል)።
- ✓ ጤና መኮንን የነበረ ባለሙያ ህክምና ተምሮ የብቃት ምዘና ፈተና አልፎ ቢመጣ፤ በመረጠው በአንዱ ብቻ የሙያ ስራ ፈቃድ ይሰጠዋል፤ በጤና መኮንን ሙያ የሙያ ስራ ፍቃድ ቢጠይቅ ህክምና ትምህርት ላይ ነበርክ ተብሎ ለተግባር ልምምድ ሊመደብ አይገባውም (በትምህርት ላይ የነበረበት ጊዜ እንደ ስራ ልምድ ይቆጠርለታል)።
- ✓ የስራ ልምድን በተመለከተ ተዛማጅ ለሆኑ ሙያዎች ባለሙያው በትምህርት ላይ የቆየበት ጊዜ ለሌላኛው ሙያ (ቀድሞ ይሰራበት ለነበረው ሙያ) የስራ ልምድ መሆን ይችላል።

<u>ምሳሌ</u>፡ በፋርማሲ ዲፕሎማ የነበረው ባለሙያ በዚሁ ሙያ ዲግሪ ተምሮ የብቃት ምዘና ፈተና አልፎ ከመጣ እና በፋርማሲ ቴክኒሽያን የሙያ ፈቃድ ከፈለገ፤ ክሊኒካል ነርስ የነበረ ጤና መኮንን ተምሮ የብቃት ምዘና ፈተና አልፎ መጥቶ በክሊኒካል ነርስ የሙያ ፈቃድ ቢጠይቅ፤ ጤና መኮንን የነበረ ህክምና ተምሮ የብቃት ምዘና ፈተና አልፎ ቢመጣና በጤና መኮንን የሙያ ፈቃድ ቢጠይቅ ወዘተ በቀጥታ በአንዱ ብቻ መውሰድ ይችላል።

2. **መጀመሪያ ከያዙት ሙያ ጋር ተዛማጅ ትምህርት ተምረው መጥተው የሙያ ስራ ፍቃድ ጥያቄ ሲያቀርቡ የሚሰጣቸው ስያሜ ለምን ከጀማሪ (Junior) እንዲጀምር ይደረጋል? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ፡-**

**የመፍትሄ ሀሳብ፡**

- ➢ ስያሜው ቀድሞ ከተሰጣቸው ስያሜ ጋር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ ባለመሆኑ መመሪያው ላይ በተቀመጠው መሰረት እንዲቀጥል ይደረግ)

3. **ከ 10 ዓመት በታችና ከ10 ዓመት በላይ ስራ አቋርጠው ቆይተው አሁን በሙያቸው መስራት የሚፈልጉት እንዴት ይስተናገዱ? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ፡**

ጤና ሚኒስቴር Ministry of Health

<u>የመፍትሄ ሀሳብ፦</u>

- እስከ 10 ዓመት ከሙያቸው የራቁትን በተመለከተ፦
  - የMPH፣ Health Education እና Environmental Health Science ባለሙያዎች ከ15 ዓመት በታች ከሙያቸው ርቀው ቢመጡ under supervision መመደብ አይጠበቅባቸውም ነገር ግን በየአመቱ የሚጠይቀውን CPD course ወስደው ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።
  - ክሊኒካል ባለሙያዎች ለምሳሌ፦ ሀኪም፣ ነርስ፣ ላቦራቶሪ ባለሙያ፣ ፋርማሲ ባለሙያ ወዘተ Under supervision መመደብ ያለባቸው በመንግስት ጤና ተቋም ሆኖ ከተቻለ ዩኒቨርሲቲ/ማስተማሪያ/ ሆስፒታል ካልሆነ ግን under supervision ከሚመደበው ባለሙያ ከፍ ያለ የትምህርት ዝግጅት ያለው ባለሙያ ባለበት ተቋም መሆን አለበት (ለምሳሌ፦ ጤና መኮንን under supervision ለመመደብ ተቋሙ ሀኪም የሚሰራበት መሆን አለበት)።
  - ከተመረቀ ከሁለት ዓመት በላይ የሆነው፣በሙያው ሳይሰራ የቆየና በተደጋጋሚ የብቃት ምዘና ፈተናውን ያላለፈ የጤና ባለሙያ የundersupervision ምደባ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል

- ከ10 ዓመት በላይ ከሙያቸው የራቁትን በተመለከተ፦

ምንም እንኳ በመመሪያ 770/2013 ላይ ከ10 ዓመት በላይ ከሙያቸው የራቁ ባለሙያዎች የሙያ ስራ ፍቃድ ማግኘት እንደማይገባቸው ቢያስቀምጥም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ በተለያዩ አካላት በቀረበ ጥያቄ መሰረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ከተደረገበት በኋላ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲደረጉ ከስምምነት ተደርሷል።

- ከ 10 — 15 ዓመት በተለያዩ ምክንያቶች ከሙያቸው ርቀው ቆይተው በሙያቸው መስራት የሚፈልጉ ጤና ባለሙያዎች በመንግስት ዩኒቨርሲቲ ስር በሚገኝ ሆስፒታል ጥብቅ ክትትል እየተደረገባቸው ከዚህ በታች በቀረበው መሰረት መስተናገድ ይችላሉ፦

  1. ምንም ሳይሰራ (የስራ ልምድ ሳይኖረው) ከ 10 — 15 ዓመት ከሙያው ርቆ ቆይቶ የሙያ ስራ ፈቃድ ጥያቄ ቢያቀርብ 1 ዓመት ከ 6 ወር (አንድ ዓመት ከስድስት ወር) under supervision እንዲሰራ፤ ሲጨርስም ሙያው የብቃት ምዘና የሚሰጥበት ከሆነ ፈተናውን ወስዶ ሲያልፍ የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲያገኝ ቢደረግ፤
  2. ከ 6 ወር እስከ 5 ዓመት ካገለገለ በኋላ ከ 10 — 15 ዓመት ከሙያው ርቆ ቆይቶ የሙያ ፈቃድ ጥያቄ ቢያቀርብ 1 ዓመት ከ 4 ወር (አንድ ዓመት ከአራት ወር) under supervision እንዲሰራ፤ ሲጨርስም ሙያው የብቃት ምዘና ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ ፈተናውን ወስዶ ሲያልፍ የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲያገኝ ቢደረግ፤
  3. ከ 5 እስከ 10 ዓመት ካገለገለ በኋላ ከ10 — 15 ዓመት ከሙያው ርቆ ቆይቶ የሙያ ፈቃድ ጥያቄ ቢያቀርብ 1 ዓመት ከ 2 ወር (አንድ ዓመት ከሁለት ወር) under supervision እንዲሰራ፤ ሲጨርስም ሙያው የብቃት ምዘና ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ ፈተናውን ወስዶ ሲያልፍ የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲያገኝ ቢደረግ፤

4. ከ 10 - 20 ዓመት ካገለገለ በኂላ ከ 10 — 15 ዓመት ከሙያው ርቆ ቆይቶ የሙያ ፈቃድ ጥያቄ ቢያቀርብ 1 ዓመት (አንድ ዓመት) under supervision እንዲሰራ፤ ሲጨርስም ሙያው የብቃት ምዘና ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ ፈተናውን ወስዶ ሲያልፍ የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲያገኝ ቢደረግ፤
5. ከ 20 ዓመት በላይ ካገለገለ በኂላ ከ 10 — 15 ዓመት ከሙያው ርቆ ቆይቶ የሙያ ፈቃድ ጥያቄ ቢያቀርብ 9 ወር (ዘጠኝ ወር) under supervision እንዲሰራ፤ ሲጨርስም ሙያው የብቃት ምዘና ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ ፈተናውን ወስዶ ሲያልፍ የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲያገኝ ቢደረግ፤
6. ባለሙያው ከ15 ዓመት በላይ ከሙያው ርቆ ቆይቶ ቢመጣ የሙያ ስራ ፈቃድ ሊሰጠው (ሊታደስለት) አይገባም፡፡

❖ ከ 10 ዓመት በታች ከሙያቸው የራቁ ባለሙያዎችን under supervision አመዳደብ በተመለከተ መመሪያ 770/2013 ሰንጠረዥ 1 ላይ በተቀመጠው መሰረት ሆኖ በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት ተስተካክሏል

❖ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠርዥ መሰረት under supervision የተመደበ የጤና ባልሙያ ልምምዱን ሲያጠናቅቅ ሙያው የብቃት ምዝና ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ ፈተናውን ተፈትኖ ሲያልፍ የሙያ ስራ ፈቃድ ይሰጠዋል

| ተ/ቁ | ባለሙያው በስራ ላይ የቆየበት ጊዜ | ባለሙያው ከስራው ተለይቶ የቆየበት ጊዜ | በበሳል ባለሙያ ስር በክትትል under supervision የሚቆበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ምንም ያልሰራ | ከሁለት እስከ ሦስት ዓመት | ለስድስት ወር |
| | ምንም ያልሰራ | ከአራት እስከ አምስት ዓመት | ለዘጠኝ ወር |
| | ምንም ያልሰራ | ከስድስት እስከ አስር ዓመት | ለአንድ ዓመት |
| 2 | ከ6 ወር አስከ 5 ዓመት | ከሁለት እስከ አራት ዓመት | ለድስት ወር |
| | ከ6 ወር አስከ 5 ዓመት | ከአምስት እስከ ስባት ዓመት | ለዘጠኝ ወር |
| | ከ6 ወር አስከ 5 ዓመት | ከስምንት እስከ አስር ዓመት | ለአንድ ዓመት |
| 3 | ከ 5 እስከ 10 ዓመት | ከሶስት እስከ አምስት ዓመት | ለሦስት ወር |
| | ከ 5 እስከ 10 ዓመት | ከስድስት እስከ ስምንት ዓመት | ለስድስት ወር |
| | ከ 5 እስከ 10 ዓመት | ከዘጠኝ እስከ አስር አመት | ለአንድ ዓመት |
| 4 | ከ10 እስከ 20 | ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት | ለሦስት ወር |
| | ከ10 እስከ 20 | ከሰባት እስከ አስር አመት | ለስድት ወር |
| 5 | ከ20 ዓመት በላይ | ከስድስት እስከ ስምንት ዓመት | ለሦስት ወር |
| | ከ20 ዓመት በላይ | ከስምንት እስከ አስር ዓመት | ለስድስት ወር |

ማስታወሻ፡ ከ6 ወር በታች አግልግሎ ከሙያው ቢርቅ ምንም ያልሰራ በሚለው ዝርዝር ውስጥ ይካተታል፡፡

ጤና ሚኒስቴር
የሰው ሀብት ልማት
Ministry of Health

4. ትምህርታቸውን ከጨረሱ ከ10 ዓመት በኋላ COC አልፈው (ነገር ግን ከ10 ዓመት በላይ ከሙያቸው ርቀው) የሚመጡትን እንዴት እናስተናግዳቸው? የሚለውን በተመለከተ፡

<u>የመፍትሄ ሀሳብ፦</u>

- COC ማለፍ የሙያ ስራ ፍቃድ ለማውጣት ራሱን የቻለ አንድ ቅድመ ሁኔታ እንጂ በራሱ በቂ ባለመሆኑ ባለሙያዎቹ ከሙያቸው የራቁበት ጊዜ ታሳቢ ሊደረግ ይገባል::

  በዚህ መሰረት፦

  1. በተለያዩ ምክንያቶች ከተመረቁ 10 — 15 ዓመት በኋላ COC አልፈው ቢመጡ ከ10 — 15 ዓመት ከሙያቸው ርቀው ቆይተው እንደመጡ ታሳቢ ተደርጎ ለ1 ዓመት ከ2 ወር (አንድ ዓመት ከሁለት ወር) under supervision በመንግስት ዩኒቨርሲቲ ስር በሚገኝ ሆስፒታል በጥብቅ ክትትል እንዲሰሩ ተደርጎ ሲጨርሱ እና ሙያው የብቃት ምዘና ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ ፈተናውን ወስደው ሲያልፉ የሙያ ስራ ፈቃድ ይሰጣቸዋል::
  2. ባለሙያው ከተመረቀ ከ15 ዓመት በኋላ COC አልፎ ቢመጣ (ከ15 ዓመት በላይ ከሙያው ተለይቶ) እና የሙያ ስራ ፈቃድ ቢጠይቅ ሊስተናገድ አይገባውም::

- ነገር ግን ከ10 ዓመት በታች ከሙያቸው ርቀው ቆይተው COC አልፈው የሙያ ስራ ፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርቡትን ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 1 መሰረት under supervision እንዲሰሩ ይደረጋል::

5. ለተወሰኑ ዓመታት ከሙያቸው የተለዩ ባለሙያዎችን ለተግባር ልምምድ /under supervision/ የት እና እንዴት እንመድባቸው? የሚለውን በተመለከተ፡

<u>የመፍትሄ ሀሳብ፦</u>

- በተራ ቁጥር 3 በተመላከተው መሰረት ቢስተናገዱ

6. ከውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ጨርሰው ነገር ግን በሙያቸው መስራት ሳይጀምሩ የሚመጡ ባለሙያዎችን ለተግባር ልምምድ /under supervision/ ለምን ያህል ጊዜ እንመድባቸው? የሚለውን በተመለከተ፡

<u>የመፍትሄ ሀሳብ፦</u>

- ከውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመጡ ባለሙያዎች ጠቅላላ ሀኪም ለ1 ዓመት (አንድ ዓመት) ፤ ሌሎች ባለሙያዎች የጥርስ ሀኪምን ጨምሮ ለ6 ወር (ስድስት ወር) ብቻ under supervision ይመደባሉ፤ ልምምዱን ጨርሰው የብቃት ምዘና ፈተና ወስደው ሲያልፉ (ሙያው የብቃት ፈተና የሚሰጥበት ከሆነ) የሙያ ስራ ፈቃድ ይሰጣቸዋል::

7. ሀገር ውስጥ ትምህርቱን የተማረ እና የሙያ ስራ ፈቃድ አውጥቶ ሲሰራ የነበረ ኢትዮጵያዊ በዚህ የትምህርት ማስረጃ እና የሙያ ስራ ፍቃድ ውጭ ሀገር በአለም



Ministry of Health

ዓቀፍ ድርጅቶች ሲሰራ ቆይቶ ቢመጣ የሙያ ስራ ፈቃድ የት እና እንዴት ነው የሚያወጣው? የሚለውን በተመለከተ፡

**የመፍትሄ ሀሳብ፡-**

- በአለም ዓቀፍ ተቋማት (WHO, UNICEF, ወዘተ) ሲሰራ ቆይቶ ኢትዮጵያ ውስጥ የሙያ ፈቃድ እድሳት ቢጠይቅ እነዚህ አለም አቀፍ ተቋማት ስራቸው በአንድ ሀገር የተገደበ ባለመሆኑ ሲሰራበት ከነበረው ሀገር ተጨማሪ የሙያ ስራ ፈቃድ ማምጣት ሳይጠበቅበት ሲሰራበት በነበረው ሙያ በፌደራል ደረጃ (በጤና ሚኒስቴር) እድሳት ይደረግለታል፡፡

8. ሀገር ውስጥ ትምህርቱን የተማረና የሙያ ስራ ፈቃድ አውጥቶ ሲሰራ የነበረ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ውስጥ በተማረው የትምህርት ማስረጃ ውጭ ሀገር የሙያ ስራ ፈቃድ አውጥቶ (ትምህርቱን ሳያሻሽል) ሲሰራ ቆይቶ ቢመጣ የሙያ ስራ ፈቃድ የት ነው የሚያወጣው? የሚለውን በተመለከተ፡

**የመፍትሄ ሀሳብ፡-**

- ሲሰራበት በነበረው ሀገር የተሰጠውን የሙያ ስራ ፈቃድ ትክክለኛነት አረጋግጦ (Authenticate አስደርጎ) ሲመጣ በፌደራል ደረጃ (በጤና ሚኒስቴር) እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

9. ሀገር ውስጥ ትምህርቱን የተማረና የሙያ ስራ ፈቃድ አውጥቶ ሲሰራ የነበረ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ውስጥ ያወጣውን የሙያ ስራ ፈቃድ ተጠቅሞ ውጭ ሀገር ሲሰራ ቆይቶ (በውጭ ሀገር የሙያ ፍቃድ ሳያወጣ) የሙያ ፈቃድ እድሳት ቢጠይቅ እንዴት እናስተናግደው?

**የመፍትሄ ሀሳብ፡-**

- ህጋዊ በሆነ ተቋም ሲሰራ የነበረ ከሆነ የስራ ልምዱን ትክክለኛነት አረጋግጦ (Authenticate አስደርጎ) ሲመጣ ለአንድ ጊዜ ብቻ በፌደራል ደረጃ (በጤና ሚኒስቴር) ይታደስለታል (ለሁለተኛ ጊዜ የድሳት ጥያቄ ቢያቀርብ ሲሰራበት ከነበረው ሀገር የተሰጠውን የሙያ ስራ ፈቃድ እንዲያቀርብ ይገደዳል)፡፡

10. ሀገር ውስጥ ትምህርታቸውን ጨርሰው አሁን ውጭ ሀገር የሚኖሩና Letter of Good Standing የሚጠይቁ ነገር ግን ቅድመ ሁኔታውን (በተቀጣጣሪ አካል መመዝገብ፣ የስራ ልምድ ማቅረብ እና በስራ ቆይታቸው ምንም አይነት የስነ ምግባር ጉድለት ያልፈፀሙና የዲሲፕሊን ጉድለት የሌለባቸው ስለመሆኑ ማስረጃ) ያላሟሉ ባለሙያዎችን በተመለከተ፡

ሀ/ ኢትዮጵያ ውስጥ የሰሩና የተመዘገቡ ነገር ግን ምንም አይነት የስነ ምግባር ጉድለት እንደሌለባቸው የሚገልፅ የስራ ልምድ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሰሩበት ከነበርው ትቋም ማቅረብ ያልቻሉ፡

**የመፍትሄ ሀሳብ፡-**

ጤና ሚኒስቴር
የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር
Ministry of Health

- ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሰሩበት ከነበረው ተቋም ባቀረቡት በደብዳቤው መሰረት ስለመመዝገቡ ብቻ የሚገልፅ Letter of Good Standing መፃፍ (የስነ ምግባር አፈጻጸምን በተመለከተ ማስረጃ አለመገኘቱን በአጽንኦት (Bold) መግለጽ)፡፡

**ለ/ ኢትዮጵያ ውስጥ በ Internship የተመዘገቡ፣ የስራ ልምድ ያላቸው ወይም ምንም ሳይሰሩ ከሀገር የወጡ፡**

**<u>የመፍትሄ ሀሳብ፦</u>**

- ባላቸው (በሚያቀርቡት) ማስረጃ መሰረት ማስረጃው ላይ የተጠቀሰው ሀሳብ ብቻ ተገልጾ ቢፃፍላቸው፡፡

**ሐ/ ኢትዮጵያ ውስጥ የሰሩ፣ የስራ ልምድ ያላቸው ነገር ግን በተቆጣጣሪ አካለ ያልተመዘገቡ**

**<u>የመፍትሄ ሀሳብ፦</u>**

- ጤና ባለሙያዎቹ እንደ ሀገር ምደባ ከመቀሙ በፊት በጤና ሚኒስቴር ተመድበው የሰሩ ከሆነ በጤና ሚኒስቴር ምደባ የተሰጠበትን ደብዳቤ እንደመነሻ በመውሰድ ይሰሩበት በነበረው ክልል ባለ ትቆጣጣሪ አካል ይስተናገዱ፡፡